የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

የጤና ሚኒስቴር

ሞዴል የማህበረሰብ መድኃኒት ቤት የአሠራር መመሪያቁጥር 362/2013

ጥር 2011 ዓ.ም

አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ

መግቢያ

ጤና ለአንድ ህብረተሰብ የአካል፣ የአዕምሮ እና የማህበራዊ ደህንነት መሠረት ሲሆን መድኃኒት ደግሞ ለጤና አገልግሎቱ ስኬታማነት ወሳኝ ድርሻ ያለው በመሆኑ፤

ሁሉንም መድኃኒቶች፣ የሕክምና መገልገያዎችና መሳሪያዎች በበቂ መጠን፣ በቅርበት፣ በተመጣጣኝ ዋጋ፣ የመድኃኒት የመሸጫ ዋጋ ጣሪያን በመወሰን፣ ቀጣይነት ባለው መልኩ እና ጥራታቸውን ጠብቀው ከበቂ መረጃ ጋር ለህብረተሰቡ በማቅረብ ገበያውን ማረጋጋትና መግራት በማስፈለጉ፤

አሁን ያለውን የመድኃኒት ግዥ ስርዓት በአግባቡ እና በተቀለጠፈ ሂደት በሀገር ወስጥ ያለውን ሀብት እና ጉልበት አሟጦ በማጠቀም አቅርቦቱን ተደራሽ እንዲሆን ማድረግ በማስፈለጉ፤

የጤና መድህን አገልግሎት ተጠቃሚው ህብረተሰብ የመድኃኒት አገልግሎቱን በተቀላጠፈ ሁኔታ የሚያገኝባቸው የመንግስት እና መንግስታዊ ያልሆኑሞዴል መድኃኒት ቤቶችን ለህብረተሰቡ ተደራሽ በሚሆኑበት ቦታዎች ማቋቋም እና ማስፋፋት በማስፈለጉ፤

የመድኃኒት አገልግሎቱ ጠንካራ የሆነ ስርዓት የተከተለ ካለመሆኑ ጋር ተያይዞ እየተከሰተ ባለው ችግር የተነሳ ህብረተሰቡ እየተጎዳ በመሆኑና ይህንንም ማስተካከል በማስፈለጉ፤

ለህብረተሰብ ጤና ስጋት የሆኑ በከፍተኛ ደረጃ የሚገሙቱ እና ገዳይ በሽታዎችን በቅርበት በመከታተል የጤና ማበልፀግና በሽታ መከላከል አገልግሎት በመስጠት በወቅቱ ወደ ጤና ተቋም በመላክ የህብረተሰቡን የጤና ችግር ማቃለል በማስፈለጉ፤

የጤና ተቋማትን የወስጥ ገቢ በማሳደግና ባለሞያዎችንም የገቢው ተጠቃሚ በማድረግ የስራ ተነሳሽነት እንዲጨምር ማድረግና የሰው ኃይል ፍልሰትን መቀነስ በማስፈለጉ፤

የጤና ተቋማት የመድኃኒት አቅርቦት እና አገልግሎት በማጎልበትና ተደራሽ በማድረግ የህብረተሰቡን እርካታ ሜጨምር በማስፈለጉ፤

በክቡር ሚኒስትሩ እና የጥምረት ኮሚቴ (Joint Steering Committee/JSC) ላይ በተሰጠው አቅጣጫ መሰረት የጤና ተቋማት የመድኃኒት አቅርቦት እና አገልግሎት በማጎልበትና ተደራሽ ለማድረግ የህብረተሰቡን እርካታ ሜጨምር በማስፈለጉ፤

በመሆኑም የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር በደንብ ቁጥር 167/2001 በአንቀጽ 15 በተሰጠው ስልጣንና ኃላፊነት መሰረት ይህንን ሞዴል የማህበረሰብ መድኃኒት ቤቶች አተገባበር መመሪያ አውጥቷል፡፡

<u>ክፍል አንድ</u>

<u>ጠቅላላ</u>

1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "የሞዴል ማህበረሰብ መድኃኒት ቤት የአሠራር መመሪያ ቁጥር 362/2013" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ወስጥ፡ -

1. ‹‹ሚኒስቴር እና ሚኒስትር›› ማለት እንደቅደም ተከተሉ የፌደራል ጤና ሚኒስቴር እና ሚኒስትር ነው፡፡

2. ‹‹መድኃኒት›› ማለት

ሀ) የሰወን በሽታ፣ የተዛባ ወይም ጤነኛ ያልሆነ አካላዊ ወይም አእምሮአዊ ሁኔታ ወይም ተያያዥ ምልክቶችን ለመመርመር፣ ለማከም፣ ለማስታገስ ወይም ለመከላከል፤

ለ) የሰወን አካላዊ ወይም አእምሮአዊ አሰራር በጠቃሚ ሁኔታ ለማስተካከል፣ ወደ ነበረበት ለመመለስ ወይም ለማሻሻል፤ ወይም

ሐ) ከምግብ በስተቀር የሰውነትን መዋቅር ወይም ማንኛውንም የሰውነትን ተፈጥሮአዊ ተግባር በጠቃሚ ሁኔታ ለማለወጥ፡፡

3. ‹‹የፌደራል ሆስፒታል›› ማለት ተጠሪነቱ ለጤና ጥበቃ ሚኒስተር የሆነ ሆስፒታል ወይም በዩኒቨርሲቲ ስር የሚተዳደር የጤና አገልግሎት መስጫ የጤና ሙያ ማስተማሪያ ሆስፒታል ነው፡፡

4. ‹‹የማህበረሰብ መድኃኒት ቤት›› (ከዚህ በኃላ ››ሞዴል መድኃኒት ቤት እየተባለ የሚጠራ››) ማለት የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ሞዴል የማህበረሰብ መድኃኒት ቤት አሠራር መመሪያ ላይ በተቀመጡት መመዘኛዎች መሰረት የሚተዳደር የመንግስት ወይም የግል ወይም መንግስታዊ ያልሆነ መድኃኒት ቤት ነው፡፡

5. ‹‹የመድኃኒት የዱቤ ሽያጭ› ማለት በሽያጭ እንዲተላለፍ የተወሰነላቸውን መድኃኒቶች ክፍያውን ወደፊት ለመፈፀም የቅድሚያ ውል በገባው አካል ስም ታሳቢ በማድረግ ለጊዜው ያለ ክፍያ ለተጠቃሚዎች ማስተላለፍ ነው፡፡

6. ‹‹የአደራ ግዥና ሽያጭ› (On consignment) ማለት ምንጩ ህጋዊ ከሆነ የመድኃኒት አቅራቢ በአደራ የመጣ መድኃኒት ወይም የህክምና መገልገያ ከመቀበሉ በፊት በሞዴል መድኃኒት ማከማቻና ሚዲያ ክፍል ወስጥ አለመኖሩን ሚጋገጥ እና ለዚሁ ቅብብሎሽ እንዲያገለግል በተዘጋጀው ቅጽ መዝግቦ በሚከብ በተወሰነ ጊዜ ወስጥ ለተሸጠው ያህል ብቻ የመገዣ ዋጋው የሚከፈል ሲሆን ሳይሸጥ የቀረ ቢኖር ግን ለአደራ ሰጪው ተመላሽ የሚሆንበት አሰራር ነው፡፡

7. ‹‹የማዕቀፍ ግዢ› (Framework Agreement) ማለት በየበጀት ዓመቱ ለሞዴል ማህበረሰብ መድኃኒት ቤቶች በአንድ ጊዜ ጨረታ የተመረጡ አቅራቢዎች ለረጅም ጊዜ መድኃኒቶችን እንዲያቀርቡ የሚደረግበት የግዥ ስርዓት ነው፡፡

8. ‹‹የመድኃኒት አቅራቢ›› ማለት ከውጭ መድኃኒትየሚያስገቡ ወይም ከአስመጪዎች ወይም ከሀገር ወስጥ አምራቾች ተቀብለው ለጤና ተቋማት ወይም ለመድኃኒት ችርቻሮ ድርጅቶች በጅምላ የሚያቀርቡ ተቋማት ናቸው፡፡

9. ‹‹ሰልጣኝ ተማሪ›› ማለት በዩኒቨርሲዎች ወይም ኮሌጆች ተመድበው በፋርማሲ ሙያ በሞዴል የማህበረሰብ መድኃኒት ቤት የተግበር ልምምድ የሚደረጉ ተማሪዎች ነው፡፡

10. ‹‹የትርፍ ሰዓት›› ማለት በማኅስት ሰራተኞች አስተዳደር ደንብ መሰረት ከተወሰነው ከመደበኛው የስራ ሰዓታት ወጪ በዕረፍት ቀናት እንዲሁም በህዝባዊ በዓላት ስራ የተሰራባቸው ጊዜዎች ወይም ሰዓታት ነው፡፡

11. ‹‹መነሻ ካፒታል›› ማለት የሞዴል መድኃኒት ቤቱን ለማቋቋምና የመድኃኒት ሽያጭ አገልግሎት ለማስጠት በተቋሙ የሚመደብ በጀት ወይም ከተለያዩ ምንጮች በብድር ወይም በእርዳታ የሚገኝ ጥሬ ገንዘብ ወይም በዱቤ የሚገኝ መድኃኒት አቅርቦት ነው፡፡

12. ‹‹የትርፍ ጣሪያ›› ማለት በዚህ መመሪያ ላይ በተቀመጠው የትርፍ ጣሪያ መሠረት መድኃኒቶችን እና የህክምና ግብአቶችን ለተጠቃሚው የሚያስተላልፉበት የመሸጫ ዋጋ ማለት ነው፡፡

13. ‹‹በመግዣ ዋጋ መድኃኒት መሸጥ›› ማለት ሞዴል መድኃኒት ቤት ለተሚጢ መድኃኒቶች በመግዣ ዋጋ ላይ ታሪፍ ሳይጨምር ለተጠቃሚው በሽያጭ ማስተላለፍ ማለት ነው፡፡

14. ‹ህጋዊ የመድኃኒት ምንጭ› ማለት አግባብ ባለው ተቆጣጣሪ አካል የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት የተሰጠው እና ወቅታዊ የንግድ ፈቃድ ያለው የመድኃኒት አምራች ወይም አስመጪ ወይም አከፋፋይ ድርጅት ሲሆን ህጋዊ በሆነ መንገድ ከአንድ ተቋም ወደ ሌላ ተቋም የሚደረግ ህጋዊ የመድኃኒት የማዘዋወር ስርዓትን ይጨምራል፡፡

15. ‹‹ሰው›› ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

16. ማንኛውም በወንድ ፆታ የተገለጸው አነጋገር ሴትንም ይጨምራል፡፡

3. የተፈፃሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ በሀገሪቱ ወስጥ በሚገኙ ሞዴል የማህበረሰብ መድኃኒት ቤት በሚያቋቁሙ የፌደራል ሆስፒታሎች እንዲሁም በዚህ መመሪያ መሰረት ለመተዳደር ፈቃደኛ በሆኑ የከነማ መድኃኒት ቤቶች፣ የቀይ መስቀል መድኃኒት ቤቶች እና የግል መድኃኒት ቤቶች ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

4. ዓላማዎች

የዚህ መመሪያ ዓላማ

1. መድሃኒቶች፣ የሕክምና መገልገያዎችና መሳሪያዎች በበቂ መጠን፣ በቅርቦት፣ በተመጣጣኝ ዋጋ ቀጣይነት ባለውና በአስተማማኝ ሁኔታ በማሟላት፣ ገበያ በሚረጋጋትና በመገራት ለህብረተሰቡ እንዲቀርቡ ማድረግ፤
2. የመድሃኒት አገልግሎት አሰጣጥ ግልፅነትና ተጠያቂነትን በማስፈን ጥራታቸው፣ ፈዋሽነታቸውና ደህንነታቸውን የጠበቁ መድሃኒቶች ለተገልጋዩ ከበቂ መረጃ ጋር በማስጠት በመድሃኒት የሚደርስን ጉዳት በመቀነስ የህብረተሰቡን ጤና ማጠበቅ፣
3. የመድሃኒት አግባባዊ አጠቃቀም በማስፈን የህብረተሰቡን ጤና ማጠበቅ፤
4. የጤና መድህን አገልግሎት ተጠቃሚ ህብረተሰብ የመድሃኒት አገልግሎቱን በተቀላጠፈ ሁኔታ የሚያገኙባቸው የመንግስት እና የግል ፋርማሲዎችን ለህብረተሰቡ ተደራሽ ለማድረግ፤
5. የጤና ተቋማት የወስጥ ገቢያቸውን በማሳደግ የሚሰጡትን የመድኃኒት አገልግሎት በማሻሻል የህብረተሰቡን እርካታ እንዲያሳድጉ ማድረግ እና የሰው ኃይል ፍልሰት መቀነስ፤

ክፍል ሁለት
ሞዴል የመድኃኒት ቤት ስለ መቋቋምና መደራጀት

5. ሞዴል የማህበረሰብ መድኃኒት ቤት ስለ መቋቋም

1. ሆስፒታሎች ባሉበት ከተማ ወይም አቅራቢያቸው በሚገኝ ከተማ ለህብረተሰቡ ተደራሽ በሆነ አካባቢ የራሳቸው የሆኑ ሞዴል መድኃኒት ቤቶችን ሊያቋቁሙ ይችላሉ፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) እንደተጠበቀ ሆኖ የሞዴል መድኃኒት ቤቶችን ሲያቋቁሙ በአቅራቢያው ሌላ ሞዴል የማህበረሰብ መድኃኒት ቤት አለመኖሩን ሚረጋገጥ ይኖርባቸዋል፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) እና (2) እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም ሞዴል መድኃኒት ቤት የሚከፈተው ከሌላ ሞዴል መድኃኒት ቤት ቢያንስ በአንድ ኪሎ ሜትር ርቆ መሆን ይኖርበታል፡፡
4. ሆስፒታሉ ከቅጥር ግቢ ውጭ ሞዴል መድኃኒት ቤት ከመከፈቱ በፊት በሆስፒታሉ ውስጥ የሚገኘውን የተሟላሽ መድኃኒት ቤት ሞዴል የማድረግ ኃላፊነት አለበት፡፡
5. ሆስፒታሉ ሞዴል መድኃኒት ቤቶችን ለመቋቋም የመነሻ ካፒታል ሊኖረው ይገባል፡፡
6. ሞዴል መድኃኒት ቤቶቹ ስራቸውን ለመጀመር የሚያስችላቸውን የመድኃኒት አቅርቦት ከመድኃኒት አቅርቦት ኤጀንሲ በዱቤ ሊያገኙ ይችላሉ፡፡
7. ማንኛውም ሞዴል መድኃኒት ቤት የመድኃኒት አገልግሎት አሠጣጡን የተቀላጠፈ ለማድረግ የሚያስችል ብቁ ሠራተኞች፣ መሳሪያዎችና ቁሳቁሶች እንዲሁም የመድኃኒት ማከማቻ፣ መቀመጫ፣ የመድኃኒት መረጃና ስለ አጠቃቀሙ የምክር አገልግሎት መስጫ ክፍሎች ለተጠቃሚው ህብረተሰብ አመቺ በሆነ መንገድ መደራጀት አለበት፡፡
8. ሞዴል መድኃኒት ቤቱን ለመቋቋም ለኦዲት ግልጽና አመቺ የሆነ አሰራር ማዘርጋት አለበት፡፡

6. መነሻ የሀብት ምንጭ

1. የሞዴል የማህበረሰብ መድኃኒት ቤት አገልግሎት መቋቋሚያ ካፒታል የሆስፒታሉ የስራ አመራር ቦርድ በሚፈቅደው መሰረት ከዚህ በታች ከተዘረዘሩት በአንዱ ወይም ከዚያ በላይ ከሆና ምንጭ በተገኘ ካፒታል ሊቋቋም ይችላል፡፡
2. ከሆስፒታሉ የወስጥ ገቢ ከሚገኝ ከወለድ ነፃ ብድር፤
3. ከመንግስት ከሚገኝ መደበኛ የበጀት ድጋፍ ወይም
4. እንዳአስፈላጊነቱ ከሌሎች ምንጮች ከሚገኝ ገቢ ሊታቋም ይችላል

7. ስለከነሜ የቀይ መስቀልና የግል መድኃኒት ቤቶች

በዚህ መመሪያ በተቀመጠው መሰረት ከነሜ የቀይ መስቀል እና የግል መድኃኒት ቤቶች ባለቤቶች መድኃኒት ቤቶቻቸውን ሞዴል ማድረግ ከፈለጉ በዚህ መመሪያ የተቀመጡትን ድንጋጌዎች በማሟላት ከሚኒስቴር መስሪያ ቤት ጋር የወል ስምምነት ሚፈራረም አለባቸው፡፡

8. ሞዴል የማህብረሰብ መድኃኒት ቤቶች አደረጃጀት

1. እያንዳንዱ ሆስፒታል የሚያቋቁማቸው ሞዴል የማህብረሰብ መድኃኒት ቤቶች የየራሳቸው ኃላፊና ሰራተኞች እንዲሁም ለአገልግሎት አስፈላጊ የሆኑ ክፍሎችና የአሰራር መሣሪያዎች ያሏቸው ራሳቸውን የቻሉ ተቋማት ሲሆኑ በሆስፒታሉ የበላይ ኃላፊ ወይም በበላይ ኃላፊው በሚወከለው የሚመራ "የማህብረሰብ መድኃኒት ቤት ሜጅመንት ኮሚቴ" ይተዳደራሉ፡፡
2. የሞዴል መድኃኒት ቤቱ አስተባበሪ ተጠሪነቱ ለሆስፒታሉ የፋርማሲ ክፍል ኃላፊ ይሆናል፡፡
3. የሞዴል መድኃኒት ቤት ሜጅመንት ኮሚቴ ተጠሪነቱ ለሆስፒታሉ ቦርድ ይሆናል፡፡
4. የጤና ሚኒስቴር የዚህን ፕሮጀክት አተገባበር በበላይነት የሚከታተል አካል ይሰይማል፡፡
5. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) እንደተጠበቀ ሆኖ የከነማ፣ የቀይ መስቀል እና የግል ሞዴል መድኃኒት ቤቶች እንደሁኔታው አመቺ የሆነ አደረጃጀት መፍጠር አለባቸው፡፡

9. የሞዴል የማህብረሰብ መድኃኒት ቤት ሜጅመንት ኮሚቴ አደረጃጀት

1. የሞዴል መድኃኒት ቤት የሜጅመንት ኮሚቴ አባላት የሆስፒታሉ የበላይ ኃላፊ፣ የፋይናንስ ኃላፊ፣ የሆስፒታሉ የፋርማሲ ክፍል ኃላፊ፣ የሰው ሀብት ኃላፊ፣ የሞዴል መድኃኒት ቤቱ ኃላፊ ይሆናሉ፡፡
2. የኮሚቴው ሰብሳቢ የሆስፒታሉ የበላይ ኃላፊ ሲሆን፣ ጸሀፊው የሞዴል መድኃኒት ቤቱ ሀላፊ፣ የሂሳብ ሹሙ ደግሞ የፋይናንስ ሀላፊው ይሆናል፡፡

ክፍል ሶስት
የሰው ሀብት አስተዳደር

10. ስለ ቅጥር አፈጻጸም ወይም የሰራተኛ አመዳደብ

1. የሞዴል መድኃኒት ቤት ኃላፊ በሆስፒታሉ ይመደባል ወይም በሆስፒታሉ የቅጥር ሂደት ማስረት ይቀጠራል፡፡
2. ሌሎች የሞዴል መድኃኒት ቤት ሰራተኞች በሆስፒታሉ ይመደባሉ ወይም በሆስፒታሉ የቅጥር ሂደት ማስረት ይቀጠራሉ፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) እና (2) የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ የሰራኞች ቅጥር በተማከተ የሲቪል ሰርቪስ ህግ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡
4. በመደበኛ የፋርማሲ አገልግሎት አሰጣጥ በእውቀታቸው፣ በችሎታቸው፣ በተነሳሽነታቸው፣ በመደበኛ የሥራ ሰዓት ባላቸው የሥራ ወጤትና በሙያ ስነ-ምግባራቸው የተሻሉ እና ፍቃደኝነታቸው እየታየ በሞዴል መድኃኒት ቤት ክፍል ወስጥ በሚወጣው የሥራ ፕሮግራም ማስረት በየተራ እየተመደቡ እንዲሰሩ ያደርጋል፡፡
5. ማንኛውም በሞዴል መድኃኒት ቤት አገልግሎት ላይ የሚሰተፍ ባለሙያ የቆጠራ ሪፖርት ላይ መፈረም ይኖርበታል፡፡
6. በዚህ ንዑስ አንቀጽ (5) የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ ወደ ሞዴል መድኃኒት ቤት የሚዛወሩ ሠራተኞች ዝወውሩ ከመድኃኒት ቆጠራ በፊት እንዲሁም ከሞዴል መድኃኒት ቤቱ የሚለቅ ወይም የሚዛወር ባለሙያ ከመድኃኒት ቆጠራ በኃላ መሆን አለበት፡፡
7. በሆስፒታሉ መደበኛ ሰዓት ወይም በተረኝነት ተመድቦ የሚሰራ ባለሙያ በተማሳሳይ ሰዓት በሞዴል የማህብረሰብ መድኃኒት ቤት መመደብ የለበትም፡
8. በሞዴል መድኃኒት ቤት ወስጥ የድጋፍ ሰጭ ሰራተኞች ምደባ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ከላይ በዚሁ ንኡስ አንቀፅ (4) በተጠቀሰው ማስረት በየተራ እንዲመደቡ ይደረጋል፡፡
9. በዚሁ ንኡስ አንቀፅ (1) እስከ (8) የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ የከነሜ የቀይ ማስቀልና የግል ሞዴል መድኃኒት ቤቶች በራሳቸው መመሪያ ሊቀጥሩ ይችላሉ፡፡

11. በፈረቃ ስለ ማስራት

ማንኛውም ሞዴል መድኃኒት ቤት የህብረተሰቡን ፍላጎት ለሟኪካትና የመድኃኒት ተደራሽነትን ለሚጋገጥ ተቋሙ ወይም መንግስት በሚወጣው ማሰረት በፈረቃ የማስራት ግዴታ አለበት፡፡

12. . የሰራተኛ መብትና ግዴታ

የሞዴል መድኃኒት ቤት ሰራተኞች መብትና ግዴታ በሲቪል ሰርቪስ ህግ ማስረት ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

13. ስለ ደመወዝና ጥቅማ ጥቅም

1. በሞዴል መድኃኒት ቤት የሚሰሩ ሰራተኞች ደመወዝ በመንግስት ሰራተኞች የደመወዝ ስኬል መሰረት ይሆናል፡፡
2) ሞዴል መድኃኒት ቤቱ በየወሩ ከሚያገኘው የተጣራ ትርፍ ላይ ተመስርቶ የትርፉን 50 በመቶ ለሆስፒታሉ፣ 35 በመቶ ለፋርማሲ ባለሙያዎች በሰሩበት ሰዓት ታሳቢ ሆኖ፤ 15 በመቶ ከስራዉ ጋር ግንኙነት ላላቸዉ ሰራተኞች እና ለአስተዳደር ክፍል በየወሩ የሚከፈል ይሆናል፡፡
3) በዚህ አንቀጽ ንዐስ አንቀጽ (2) የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ የአከፋፈል ዝርዝር በተመለከተ የሆስፒታሉ ሜጅመንት የሚወሰን ይሆናል፡፡
4) ከሆስፒታሉ ድርሻ ላይ ለመድኃኒት ቤቱ ማስፋፊያ እና ማጠናቀርያ ሊወል ይችላል፡፡
5) በዚህ አንቀጽ ንዐስ አንቀጽ (2) የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ ለሰራተኞች የትርፍ ክፍያ የሚጀመረው የሶስት ወር ቆጠራና ኦዲት ከተጠናቀቀ በኋላ ሆኖ በሶስቱ ወራት በተገኘው ትርፍ መሰረት ለቀጣዩ ሶስት ወራት በየወሩ የሚከፈል ይሆናል፡፡
6) በዚህ አንቀጽ ንዐስ አንቀጽ (2) እንደተጠበቀ ሆኖ ቅመማ ለሚሰሩ ባለሙያዎች ከአገልግሎት ክፍያ ላይ 50 በመቶ የሚከፈል ይሆናል፡፡
7) ሞዴል መድኃኒት ቤቱ የሚከፈትበት የስራ ፍቃድ ሚረጋገጫ የምስክር ወረቀት ክፍያ ሊኖረው ይችላል፡፡
8) ከላይ በንኡስ አንቀፅ (3) የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ ክፍያው የሚፈፀመው ከኦዲት ሪፖርት እና ሪፖርቱ በሆስፒታሉ ሜጅማንት እና በአማራር ቦርድ ሲፀድቅ ይሆናል፡፡

14. ስለ ስራ ሰዓት

ማንኛውም ሞዴል መድኃኒት ቤት በሚገኝበት አካባቢ ወይም ሰፈር የሚኖረውን ህብረተሰብ ፍላጎት በማገናዘብ የሚከፈት ሆኖ ከዚህ በታች በተዘረዘረው መስፈርት መሰረት አገልግሎት ሊሰጥ ይችላል፡፡

1) ዘወትር ከሰኞ እስከ አርብ በመንግስት የስራ ሰዓት አገልግሎት ይሰጠል በተጨማሪም ከመንግስት የስራ ሰዓት ውጭ እንዲሁም ዘወትር ቅዳሜ እሁድ እና በህዝባዊ በዓላት ወቅት ቢያንስ እስከ ምሽቱ 4፡00 ሰዓት አገልግሎት መስጠት አለበት፤
2) ከላይ በንዐስ አንቀፅ (1) የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ እንደአስፈለጊነቱ መንግስት በሚያወጣው ፈረቃ መሰረት ቅዳሜ እሁድ እና የህዝባዊ በዓላትን ጨምሮ 24 ሰዓት አገልግሎት ሊሰጡ ይችላሉ፡፡
3) ከላይ የተጠቀሱት አንቀፆች (2) እና (3) እንደተጠበቀ ሆኖ መድኃኒት ቤቱ የሚከፈትበትንና የሚዘጋበትን ሰዓቶች የተቋሙ ሜጅማንት ሊወስን ይችላል፡፡

15. ስለ ስልጠና

የሞዴል መድኃኒት ቤቱ ሰራተኞች ለስራው አስፈላጊ የሆኑ የስራ ላይ ስልጠና ማግኘት ያለባቸው ሲሆን ይህንንም ስልጠና ሆስፒታሉ ማሟቸት አለበት፡፡

ክፍል አራት
ስለ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ አሰጣጥ

16. የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት አሰጣጥ

1. ማንኛውምሞዴል መድኃኒት ቤት አገልግሎት መስጠት ከመጀመሩ በፊት አግባብ ካለው ተቆጣጣሪ አካል የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ማግኘት አለበት፡፡
2. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1) የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ ስለ ብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት አሰጣጥ፣ ይዘት፣ የሚቀመጥበት ቦታ፣ እድሳት፣ ለውጥ፣ ምትክ አሰጣጥ እና ቅድመ ፈቃድ ኢንስፔክሽን ሂደት በተሰጠው ስልጣንና ኃላፊነት መሰረት አግባብ ያለው ተቆጣጣሪ አካል በሚያወጣው ህግ መሰረት ይሆናል፡፡
3. ማንኛውም የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ያገኘ መድኃኒት ቤት በዚህ መመሪያ የተቀመጡትን መስፈርቶች አሟልቶ ሲገኝ ሞዴል መድኃኒት ቤት መሆኑን የሚያረጋግጥ የምስክር ወረቀት አግባብ ካለው ተቆጣጣሪ አካል ይሰጠዋል፡፡
4. ማንኛውም ሞዴል መድኃኒት ቤት ደረጃውን የጠበቀ የመድኃኒት እደላና ምክር አገልግሎት፣ የመድኃኒት ቅመማ አገልግሎት፣ ታካሚ ተኮር የፋርማሲ አገልግሎት፣ የጤና ማበልጸግና በሽታ መካላከል አገልግሎት እና የመድኃኒት መረጃ አገልግሎት መስጠት አለበት፡፡

17. ስያሜ

ማንኛውም መድኃኒት ቤት "ሞዴል" የሚል ስያሜ ከፌደራል ጤና ሚኒስትር ወይም ከክልል ጤና ጥበቃ ቢሮ ብቻ ይገኛል፡፡

ክፍል አምስት
የህንፃ ዲዛይንና የአካባቢ ሁኔታ፣ባለሞያና የአስፈላጊ ግብዓት ማሟላት

ስለ ህንፃው ዲዛይንና የአካባቢ ሁኔታ አግባብ ባለው የተቆጣጣሪ አካል ያወጣው ህግ እንደተጠበቀ ሆኖ የሚከተሉትን ማሟላቶች ማሟላት አለበት፡፡

18. ስለ ህንፃ ዲዛይንና የአካባቢ ሁኔታ

1. ማንኛውም ሞዴል መድኃኒት ቤት ራሱን የቻለ እና ከማንኛውም ሌላ አገልግሎት ከሚሰጥ ክፍል ጋር በበር ወይም በመስኮት የማይገናኝ መሆን አለበት፡፡
2. ማንኛውም ሞዴል መድኃኒት ቤት የሚከተሉት ክፍሎች እና ቦታዎች ሊኖሩት ይገባል
    1. የመድኃኒት ሽያጭ ክፍል፤ የገንዘብ ተቀባይ ቦታ እና ልዩ የምክር አገልግሎት መስጫ ቦታ
    2. የመድኃኒት ማከማቻ ክፍል
    3. የመድኃኒት መቀመሚያ ክፍል
    4. የመድኃኒት ሚኒጃ መስጫ የመድኃኒት ቤት ኃላፊ (በጋራ)
    5. የመድኃኒት ቤት ሂሳብ ባለሞያ ቢሮ
    6. የመድኃኒት ቤቱ መጸዳጃ ክፍል (የሴትና የወንድ)
3. የምክር አገልግሎት የሚሰጥበት ክፍል የታካሚዎችን የግል ነፃነት የጠበቀ እና ከሚረብሽ ድምፅ ነፃ መሆን አለበት
4. የመድኃኒት ሽያጭ ክፍል ካውንተር የታካሚዎችን የግል ነፃነት እና ምስጢር ሊጠብቅ በሚችል አኳኋን መሰራት አለበት
5. የመድኃኒት ቤቱ መግቢያ፣ ሽያጭ ካውንተር እና በሮች ለአካል ጉዳተኞች አመቺ መሆን አለባቸው
6. መድኃኒት ቤቱ ከሌሎች አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ግልፅ በሆነ ሁኔታ መለየት የሚችል ሆኖ መሰራት አለበት
7. የመድኃኒት ሽያጭ እና ማከማቻ ክፍል እንዲሁም የሽያጭ ባልኮንን በተመለከተ አግባብ ያለው ተቆጣጣሪ አካል በአስቀመጠው ማሟላት ይሆናል፡፡

19. ስለመድኃኒት ቅመማ

1. ማንኛውም ሞዴል መድኃኒት ቤት የቅመማ አሰራር ስርዓት ሊኖረው ይገባል
2. ማንኛውም ሞዴል መድኃኒት ቤት መድኃኒት የሚቀምመው በሐኪም በታዘዘ የመድኃኒት ማዘዣ ወረቀት መሰረት መሆን አለበት

20. ስለ ባለሞያ

1. የሞዴል የማህብረሰ መድኃኒት ቤት አስተባበሪ በሞያው ቢያንስ ሶስት አመትና ከዚያ በላይ ተያያዥ በሆነ የስራ ዘርፍ ያገለገለ ፋርማሲስት መሆን አለበት፡፡
2. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1) የተቀመጠው እንደተጠበቀ ሆኖ የሚከተሉት ተጨማሪ ባለሞያዎች መኖር አለባቸው
   - (ሀ) አምስት ፋርማሲስቶች
   - (ለ) ዲራግስት (እንደስፈላግነቱ)
   - (ሐ) አንድ የመድኃኒት ሂሳብ ባለሞያ
   - (መ) ሁለት የገንዘብ ተቀባዮች
   - (ሠ) አንድ የፅዳት ሰራተኛ
   - (ረ) አንድ የጉልበት ሰራተኛ (Porter) (እንደስፈላግነቱ)
   - (ሸ) ሁለት የጥበቃ ሰራተኞች
3. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1) እና (2) የተቀመጠው እንደተጠበቀ ሆኖ መድኃኒት ቤቱ የሚያስፈልጉ ባለሞያዎች በቁጥር እና በአይነት የስራ ጫና በማጥናት የሚሟሉ ይሆናል፡፡

21. አስፈላጊ ግብአትና ቁሳቁስ

ሞዴል መድኃኒት ቤቱ አባሪ የተደረጉትን አስፈላጊ ግብዓቶች እና ቁሳቁሶች ማሟላት አለበት፡፡

ክፍል ስደስት
ስለ መድኃኒት ግዥ፣ ክምችት፤ ስርጭት እና ሽያጭ

22. ስለ መድኃኒት ግዥ

1. ማንኛውም ሞዴል መድኃኒት ቤት የመድኃኒት ግዢ ሊፈፀም የሚችለው አግባብ ካለው ተቆጣጣሪ አካል ፈቃድ ከተሰጠው የመድኃኒት አቅራቢ ድርጅት ነው፡፡
2. ለሞዴል መድኃኒት ቤቱ የመድኃኒት ግዥን የሚፈፀመዉና የሚከበው የፋርማሲ ባለሙያ የተለያዩ መሆን አለባቸው፡፡
3. ማንኛውም ሞዴል መድኃኒት ቤት የበጀት ዓመቱን የመድኃኒት ፍላጎት ዝርዝር በሚኒ ላይ የተመሰረተ፣ የአካባቢውን የበሽታ ስርጭት ያገናዘበ እና ነፍስ አድን ለሆኑ መድኃኒቶች ቅድሚያ በመስጠትና በጤና መድኅን ሽፋን ለታቀፉ መድኃኒቶች ትኩረት በመስጠት በዓይነት ለይቶ ማዘጋጀት ይጠበቅበታል፡፡ ማዘርዝሩም በየደረጃው ለሚቋቋመው የሞዴል መድኃኒት ቤት ማስተባበሪያ አካል እና ለመድኃኒት አቅርቦት ኤጀንሲ ይላካል፡፡
4. ሞዴል መድኃኒት ቤቱ የመድኃኒት አቅርቦት ኤጀንሲ አወዳድሮ ካሳወቀቸው አሸናፊ አቅራቢዎች ላይ ግዥ ይፈጽማል፡፡
5. ማንኛውም ሞዴል መድኃኒት ቤት በአካባቢው ተፈላጊ የሆኑት መድኃኒቶችን የማቅረብ ግዴታ አለበት፡፡
6. ሞዴል መድኃኒት ቤቶቹ በየአራት ወሩ ከአሸነፉ አቅራቢ ድርጅቶች ለአራት ወራት የሚያስፈልጓቸውን መድኃኒቶች በመጠን አቅራቢው እስከ መድኃኒት ቤቱ ድረስ እንዲያመጣላቸው ያዝዛሉ፣ የግዢ ማጠየቂያ በማቅረብ መድኃኒቱን ተቀብለው ገቢ ያደርጋሉ፣ ገቢ ያደረጉበትን ሰነድ ዋናውን ቅጅ ለሚያስተዳድራቸው ሆስፒታል ይልካሉ፡፡
7. አቅራቢ ድርጅቱ ለሚያቀርባቸው መድኃኒቶች መድኃኒቶቹን ባስገባ በአንድ ወር ጊዜ ወስጥ በስምምነቱ ማስረት ክፍያ ከሆስፒታሉ ይቀበላል፡፡
8. ሞዴል መድኃኒት ቤቱ በማእቀፍ ግዥ ያልተካተቱ ወይም ያልቀረቡ መድኃኒቶች ካስፈለጉት ሌሎች የሀገሪቱ የግዥ ዘደዎችን ተጠቅሞ መግዛት ይችላል፡፡

23. ስለመድኃኒት ክምችት

1. ማንኛውም መድኃኒት ወደ መጋዘን ከመግባቱ በፊት የተጠየቀው አይነትና መጠን መሆኑን፣ ያልተበላሸ እና የአገልግሎት ጊዜው ያላለፈ መሆኑ ሚረጋገጥ አለበት፣
2. ሞዴል መድኃኒት ቤቶች መድኃኒቶችን የሚጠይቁት፣ ገቢ እና ወጭ የሚያደርጉት፣ እጅ በእጅ ወይም በዱቤ የሚሸጡት ለዚሁ አላማ ተብሎ በፌደራል የገንዘብ ሚኒስቴር ፈቃድ ለጤና ግብአቶች ብቻ ተብሎ በታተሙት ቮቸሮች፣ ቅጻቅጾች፣ ደረሰኞች እና መዝገቦች መሆን አለበት፡፡

3. ማንኛውም ሞዴል መድኃኒት ቤት ገቢ ያደረጋቸውን መድኃኒቶች ለዚሁ ዓላማ ተብሎ ደረጃውን ጠብቆ በተዘጋጀ የመድኃኒት ማዝን እንደየመድኃኒቶቹ ባህሪ በተገቢው ሁኔታና ስርዓት ተሰድረው መቀመጣቸውን ሚረጋገጥ አለበት፡፡
4. ማንኛውም ሞዴል መድኃኒት ቤት የመድኃኒት ክምችት እና እንቅስቃሴን ለመከታተልና ለመቆጣጠር የሚያስችል ቢን ካርድ፣ ስቶክ ካርድ ወይም ዘመናዊ ሶፍት ዌር በመጠቀም ክምችቱን በአግባቡ መከታተል አለበት፡፡
5. ማንኛውም የመድኃኒት ባለሙያ የሚያዛቸውን መድኃኒቶች በጠቀሜታ ጊዜያቸው ቅደም ተከተል መሰረት መድርደርና ቀድሞ የአገልግሎት ጊዜ የሚያልፍባቸውን በቅደም ተከተላቸው ጥቅም ላይ እንዲወሉ ሚድረግ አለበት፡፡
6. ማንኛውም ሞዴል መድኃኒት ቤት በማንኛውም ወቅት ከአራት ወራት ፍጆታ በላይ ክምችት ሚያዝ የለበትም፤ ከአቅም በላይ በሆነ ሁኔታ ካልሆነ በስተቀር ከአንድ ወር ፍጆታ በታች ክምችት ሚያዝንም አይፈቀድለትም፡፡
7. ማንኛውም የመድኃኒት ባለሙያ የማጠቀሚያ ጊዜ ያለፈባቸውን እና በልዩ ልዩ ምክንያት አገልግሎት ሊሰጡ የሚችሉ መድኃኒቶችን፣ አገልግሎት ከሚሰጡ መድኃኒቶች ለይቶ ሚስቀመጥና በወቅቱ ሪፖርት የሚድረግና እንዲወገዱ የሚስደረግ ኃላፊነት አለበት፡፡
8. ማንኛውም የመድኃኒት ባለሙያ በስሙ እንዲያስተዳድራቸው የተሰጡትን መድኃኒቶች የክምችት ግምገማ በማካሄድ የክምችት ዕብጠትንና ማሳትን በወቅቱ በማለየት አስፈላጊው እርምጃ እንዲወሰድ ሚስደረግ አለበት፡፡
9. ማንኛውም የሞዴል መድኃኒት ቤት ኃላፊ በክምችት ግምገማ ሪፖርት መሰረት የክምችት ዕብጠት ሲገኝ የሚስተዋወቅ፣ በተመጣጣኝ ዋጋ የመቀየር ወይም የማመለስ እርምጃዎች እንዲወሰዱ ያደርጋል፡፡
10. ማንኛውም የሞዴል መድኃኒት ቤት ኃላፊ በክምችት ግምገማ ሪፖርት መሰረት የክምችት ማሳት ሲገኝ ግዢ የሚከናወን፣ በዝውውር የማግኘት፣ በብድር የመዋስና የማሰሉት እርምጃዎች እንዲወሰዱ ያደርጋል፡፡

24. ስለመድኃኒት ስርጭት

1. የሞዴል መድኃኒት ቤት ማዝን ክፍል ባለሙያ የመድኃኒት ጥያቄ በዲስፔንሰር ፋርማሲስት በማጠየቂያ ቅጽ ተሞልቶ እና በሞዴል መድኃኒት ቤቱ ኃላፊ ወይም ተወካዩ ተፈቅዶ ሲቀርብለት በቀረበው መረጃ መሰረት ፍጆታቸውን በሚስላት የሚያስፈልገውን ማጠን በመድኃኒት ወጭ ደረሰኝ ማዝግቦ ወጪ ሚድረግ አለበት፡፡
2. መድኃኒት ገቢ የተደረገባቸው፣ የተጠየቀባቸው እና ወጪ የተደረገባቸው ሰነዶች እንደየአግባቡ በመድኃኒት ማዝን ኃላፊ እና የመድኃኒት ሂሳብ ባለሙያ እጅ በአግባቡ ፋይል ተደርገው የፋይናንስ ህግ በሚያዝዘው መሰረት ሚያዝ እና ለሚስመከታቸው ክፍሎች ሚስራጨት አለባቸው፡፡

3. ማንኛውም መድኃኒት ከመጋዘን ውጭ በሚደረግበት ጊዜ አሰራሩ የማጠቀሚያ ጊዜያቸው ቀድሞ የሚያበቁትን መድኃኒቶች ቅድሚያ ወጪ በሚድረግ መርህ ላይ የተመሰረተ መሆን ይኖርበታል፡፡

4. ማንኛውም መድኃኒት ከመጋዘን ወጪ ሲሆን፣ ወደ መጋዘን ገቢ ሲደረግ፤ የማጠቀሚያ ጊዜው አልፎ፤ ጉዳት ደርሶበት ወይም የምርት እንከን ተገኝቶበት ከክምችት ሲለይ እንዲሁም በቆጠራ ጊዜ ወዲያውኑ በክምችት መከታተያ ካርዶች (ቢን ካርድ፣ ስቶ ክካርድ ወይም ኤልክትሮኒክ ቢን ካርድ) ላይ መመዝገብ አለበት፡፡

25. ስለመድኃኒት ሽያጭ

ማንኛውም የሞዴል መድኃኒት ቤት መድኃኒቶችን ለተጠቃሚው የእጅ በእጅ ሽያጭ፣ በዱቤ ወይም በጤና መድህን ሽፋን ሊሰጡ ይችላሉ፡፡

ሀ. መድኃኒትን እጅ በእጅ ስለመሸጥ

1. በሞዴል መድኃኒት ቤቶች የእጅ በእጅ የመድኃኒት ሽያጭ የሚከናወነው ለዚሁ ሲባል በሚታተም የእጅ በእጅ የመድኃኒት ሽያጭ ማሰብሰቢያ ደረሰኝ መሆን ይኖርበታል፡፡

2. ማንኛውም ሞዴል መድኃኒት ቤት ለተጠቃሚው መሸጥ ያለበት ከ25% ባልበለጠ የትርፍ ምጣኔ ሲሆን የመድኃኒቶቹ ዋጋም በዝርዝርና በግልጽ በሚታይ ሁኔታ ለተጠቃሚው ማስጠፍ ይኖርበታል፡፡

3. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (2) የተገለጸው ለመድኃኒት እና የተለያዩ ቅመሞችን ያጠቃልላል

4. ለህብረተሰቡ በጣም አስፈለጊ የሆኑ አንድንድ መድኃኒቶች በሆስፒታሉ ሜጅምንት ተወስኖ ለማህብረሰቡ መድኃኒት ቤት በህጋዊ ደብዳቤ ዋጋቸው ተገልፆ በመግዣ ዋጋ እንዲሸጡ ሊደረግ ይችላል፡፡

5. ማንኛውም የእጅ በእጅ የመድኃኒት ሽያጭ የተከናወነበት ደረሰኝ በሶስት ቅጅ ተዘጋጅቶ ዋናው ለተገልጋዩ፣ የመጀመሪያው ቅጅ ለገንዘብ ተቀባይ ሲሰጥ ሁለተኛው ቅጅ ደግሞ ከሰነዱ ጋር መቀመጥ አለበት፡፡

6. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) እንደተጠበቀ ሆኖ ዘመናዊ ኤሌክትሮኒክ የመረጃ ስርዓት የሚጠቀሙ ሞዴል መድኃኒት ቤቶች የእጅ በእጅ የመድኃኒት ሽያጭ ደረሰኝ ለተገልጋዩ በመስጠት ስርዓቱ በሚፈቅደው መሰረት የሽያጭ መረጃ መያዝ አለባቸው፡፡

7. የእጅ በእጅ ሽያጩን ለማከናወን የተመደበ የመድኃኒት ባለሙያ በሽያጭ ደረሰኙ ላይ የተመለከቱትን የመድኃኒቱን ኮድ፣ የመድኃኒቱን ስም፣ የመድኃኒቱን መጠን፣ የችርቻሮ ዋጋ፣ ድምር እና ሌሎች አስፈላጊ መረጃዎች መዝግቦ መሆን አለበት፡፡

8. የመድኃኒት ሂሳብ ባለሙያ የዕለት የሽያጭ ማጠቃለያ ለዚሁ አላማ መድኃኒት ቤቱ በሚያዘጋጀው ቅጽ መሰረት መስራት አለበት

9. በብልጫ ወይም በጉድለት የተሸጡ መድኃኒቶች ካሉ በመድኃኒት ሂሳብ ባለሙያው በየዕለቱ ተለይተው በማጠቃለያ ሪፖርት ወስጥ መካተታቸዉን እና በፊርማ ሚረጋገጣቸወን የሞዴል መድኃኒት ቤት ኃላፊው መከታተል አለበት፡፡

10. ማንኛወም ሞዴል መድኃኒት ቤት ገንዘብ ተቀባይ የሚቀርበወን የእያንዳንዱን የሽያጭ ደረሰኝ የነጠለ እና የጠቅላላ ድምር የሂሳብ ስሌት በፊርማው ሚረጋገጥ አለበት፡፡

11. ማንኛወም ሞዴል መድኃኒት ቤት የሂሳብ ባለሙያው የሚሰራው የዕለት ሽያጭ ማጠቃለያ እና ባንክ የገባው የዕለት የገንዘብ ማጠን ሚረጋገጫ (Bank Slip) ተመሳሳይ መሆኑን ማገናዘብ ይጠበቅባቸዋል፡፡

ለ. መድኃኒትን በዱቤ ወይም በጤና መድህን ሽፋን ስለማሸጥ

1. ማንኛውም አካል በዱቤ ወይም በጤና መድህን ሽፋን የመድኃኒት አገልግሎት ሲጠይቅ ቀደም ብሎ ከሞዴል መድኃኒት ቤቱ ጋር የዱቤ አገልግሎት ውል የፈጸመ ወይም የጤና መድህን ሽፋን ያለው መሆኑ ሚረጋገጥ ይኖርበታል፡፡
2. በዚህ አንቀፅ ንኡስ አንቀፅ (1) የተገለጸዉ እንደተጠበቀዉ ሆኖ የመድኃኒት ባለሞያው የመድኃኒቱን ስም፣ ማጠን፣ አይነት፣ ጥንካሬ፣ የእሽግ ማጠን፣ የመድኃኒት ኮድ፣ የታካሚውን ካርድ ቁጥር፣ የጤና መድህን ሽፋን ካለው የጤና መድህን ማለያ ቁጥር እና የነጠለና ጠቅላላ ዋጋ መመዝገብና ተጠቃሚውን ወይም አስታማሚውን አስፈርሞ ማስጠት አለበት፡፡
3. ማንኛውም የመድኃኒት ሂሳብ ባለሞያ በየቀኑ በዱቤ ወይም በጤና መድህን ሽፋን የተሸጡ መድኃኒቶችን ከዱቤ ሽያጭ ቀሪ ጥራዝ ወይም ከመዝገቡ ላይ ለቅሞ የነጠለና የጠቅላላ ዋጋቸውን በሚረጋገጥ የዱቤወሉን በፈጸመው አካል ወይም የጤና መድህን ተቋም ስም ሂሳቡን በዱቤ ሽያጭ ማጠቃለያ ደረሰኝ ማስራት አለበት፡፡
4. በዱቤ ወይም በጤና መድህን ሽፋን ለተሸጡ መድኃኒቶች የሐኪም ማዘዣ ወረቀቶች የዱቤ ውል በገቡት ተቋማት እና የመድህን ሽፋን በሰጠው ተቋም ስም ፋይል መደረግ ይኖርባቸዋል፡፡
5. ማንኛውም ሞዴል መድኃኒት ቤት ለመድህን ሽፋን አገልግሎት ሲሰጥ ከ25% ባልበለጠ የትርፍ ምጣኔ ሲሆን የመድኃኒቶቹ ዋጋም በዝርዝርና በግልጽ በሚታይ ሚልኩ ለተጠቃሚዉ ማስጠፍ ይኖርበታል፡፡
6. በዚህ አንቀጽ የተደነገጉት እንደተጠበቁ ሆነዉ መድኃኒት በጤና መድህን ሽፋን ሲሸጥ ሌሎች የጤና መድህን ሽፋን ደንቦችና መመሪያዎችን የተከተለ መሆን ይኖርበታል፡፡

26. መድኃኒት አዘዋወር ስለማጠቀም

1. ማንኛውም ሞዴል መድኃኒት ቤት በኃላፊዎች ደረጃ በሚደረግ የጽሁፍ ስምምነት መሰረት ከፍጆታ በላይ የሆነ ክምችት ሲኖር፤ አጭር የማጠቀሚያ ጊዜ የቀራቸው መድኃኒቶች ሲኖሩ ወይም የክምችት እጥረት ሲኖር የመድኃኒቶችን የገቢና ወጪ ስርዓት ተከትሎ መድኃኒቶችን ከሌላ ተቋም ሊቀበል፤ ሊሸጥ ወይም ተመሳሳይ ዋጋ ባለው ሌላ መድኃኒት ሊለወጥ ይችላል፡፡
2. በዚህ አንቀፅ ንኡስ አንቀፅ (1) የተገለጸዉ እንደተጠበቀዉ ሆኖ ለመድኃኒት ዝወውር አፈጻጸም በተዘጋጀው መመሪያ መሰረት ማስፈጸም ይችላል፡፡

27. የፋይናንስ አስተዳደር እና ማዝገብ አያያዝ

1. ሞዴል መድኃኒት ቤት የየራሱ የባንክ አካዉንት ይኖረዋል፡፡
2. የባንክ አካዉንቱ በሆስፒታሉ ስራ አስኪያጅ እና በፋይናንስ ክፍል ኃላፊው ፊርማ ይንቀሳቀሳል፡፡
3. በየቀኑ ከዱቤ ወይም ከእጅ በእጅ የመድኃኒቶች ሽያጭ የተሰበሰበ ገንዘብ ማጠቃለያ ተሰርቶለት በተከፈተለት አካዉንት በየዕለቱ ገቢ መደረግ ይኖርበታል፡፡

4. የእለቱ ሽያጭ ማጠቃለያ ሲሰራ በማነስ ወይም በማበለጥ የተሰበሰበ ገንዘብ የተገኘ እንደሆነ ለዚሁ ማካካሻ የተቀማጠ ገንዘብ ካለ ከተቀማጠው ገንዘብ ወይም ገንዘብ ከሌለ ደግሞ ከጎደለበት ግለሰብ ከወርሐዊ ደመወዙ በታሳቢ ተቀናሽ በማድረግ ሂሳቡ እንዲታረቅ ይደረጋል፡፡

ክፍል ሰባት
ስለመድኃኒቶች አያያዝና አገልግሎት አሰጣጥ

28. ስለመድኃኒት አያያዝ

ማንኛወም የመድኃኒት ባለሙያ

1. መድኃኒቶች እንደየባህሪያቸው በተመደበለት መደርደሪያ በተገቢው ሥፍራ፣ የእርጥበት መጠን፣ የሙቀት መጠንና ከቀጥታ የፀሀይ ብርሀን የማጠበቅ ደረጃ ተፈላጊወን የጥንቃቄ ማስፈርት አሟልተው ለተወሰነላቸው የአገልግሎት ጊዜ መቀመጣቸወን ሚረጋገጥ፣ የአገልግሎት ማጠቀሚያ ጊዜያቸወን ሚከታተል፣ የዋጋ ዝርዝራቸው በሚታይ ቦታ ማለጠፍ፣ የማለያ ኮድ በሚታይ ሁኔታ ከላያቸው ላይ መጻፍ አለበት፣
2. የሚይዛቸወን መድኃኒቶች በጠቀሜታ ጊዜያቸው ቅደም–ተከተል ማስረት ቀድሞ የአገልግሎት ጊዜ የሚያልፍባቸወን ቀድሞ ማውጣት ወይም በጥቅም ላይ እንዲወሉ ሚድረግ አለበት፣
3. ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ለመድኃኒቶች አያያዝ አስጊ ሁኔታ ሚፈጠሩን የተረዳ እንደሆነ፣ ወይም ጥቅም ላይ ሳይወሉ የማጠቀሚያ ጊዜያቸው ያልፋል ብሎ ካሰበ፣ ይህንኑ አደጋ ለሚሚከተው የበላይ ሀላፊ በፅሑፍ የማስወቅ ግዴታ አለበት።
4. የማጠቀሚያ ጊዜ ያለፈባቸወንና በልዩ ልዩ ምክንያት አገልግሎት ሊሰጡ የሚችሉትን መድኃኒቶች አገልግሎት ከሚሰጡት ለይቶ፤ መዝግቦ ሚስቀመጥ እና ለሚሚከተው የበላይ ኃላፊ ማስወቅ አለበት፣
5. ተቀጣጣይነት ያላቸወን ወይም ሌሎች መድኃኒቶችን ለበክሉ የሚችሉ ኬሚካሎችን ከሌሎች መደበኛ መድኃኒቶች ለይቶ ሚስቀመጥአለበት
6. በዚህ አንቀጽ ከተራ ቁጥር 1 እስከ 5 የተቀማጡት እንዳሉ ሆነው ሙያው እና የሙያው ስነምግባር የሚጠይቃቸወን ግዴታዎች ሚክበር ይኖርበታል፡፡

29. ስለመድኃኒት ዕደላና ምክር አገልግሎት

ማንኛወም የመድኃኒት ባለሙያ፡

1. አግባብነት ያለው የመድኃኒት ዕደላ (Good Dispensing Practice) የአሰራር ስርዓትን ማስረት በሚድረግ ማስራት አለበት
2. ያለሐኪም ትዕዛዝ (ፕሪስክሪፕሽን) እና በሀገር አቀፍ ከወጣው ደረጃው የጠበቀ የመድኃኒት ማዘዣ ወረቀት ወጪ መድኃኒት ሚሸጥ የለበትም፡ ሆኖም ያለሐኪም ትዕዛዝ (OTC) እንዲሸጡ የተዘረዘሩ መድኃኒቶችን አይጨምርም፡
3. የተለያዩ የወባት ማጠበቂያ፤ ቫይታሚኖች እና ንጥረነገሮች (Minerals) ሊያቀርብ ይገባል
4. መድኃኒቶች ለታካሚ ወይም ለደንበኛ ከማታደላቸው በፊት የመድኃኒት ማዘዣ ወረቀቱ ህጋዊነት፣ ትክክለኛነት መሆኑን ማምገም አለበት

5. የቀረበለትን የመድኃኒት ማዘዣ ወረቀት ትክክለኛነት ከተጠራጠረና የተገልጋይ ደህንነት አደጋ ላይ የሚጥል ማስሎ ከታየዉ ያዘዘዉን የጤና ባለሙያ በማንኛውም መንገድ አግኝቶ ማማከር አለበት፡፡

6. የመድኃኒቶች ትክክለኛ ስም፣ የተጠቃሚ ስም፣ የመድኃኒቱን አወሳሰድ፣ ጥንካሬ፣ ለምን ያህል ጊዜ እንደሚወሰድ እና ማጠን በግልፅ ተጽፎና አግባብነት ባለው ማሸጊያ ታሽጎ ለትክክለኛው ተጠቃሚ ማስጠት አለበት፡፡

7. የሚታደለዉን መድኃኒት በተመለከተ ተጓዳኝ ችግሮች፣ ከምግብና ማጠጥ እንዲሁም ከሌሎች መድኃኒቶች ጋር ስላለው ተቃርኖ፤ የአቀማመጥ ሁኔታና የመሳሰሉት አስፈላጊ መረጃዎች በፅሁፍ እና በቃል ማስጠት አለበት፡፡

8. መድኃኒቶችን ሲያድል እና የምክር አገልግሎት ሲሰጥ በተቆጣጣሪ አካል በተሰጠ የሙያ ደረጃው በሚፈቅድለት ብቻ መሆን አለበት፡፡

9. የመድኃኒት ማዘዣ ወረቀቶች ልዩ ቁጥጥር ለሚያስፈልጋቸዉም ሆነ ለሌሎች መድኃኒቶች ስልጣን የተሰጠው አካል ያወጣው መመሪያ በሚያዘው መሠረት በአግባቡ ፋይል አድርጎ ለተወሰነላቸው ጊዜ ያህል የማስቀመጥ ኃላፊነት አለበት

10. በፍጥነት የሚዛመቱ ተላለላፊ በሽታዎች፣ የህመም ምልክት ሳያሳዩ በድንገት የሞት አደጋ ሊያደርሱ የሚችሉ ስር የሰደዱ በሽታዎችን እና ሌሎች ለህብረተሰብ ጤና ስጋት የሆኑ በሽታዎችን በቅርበት በመከታተል እና ተገቢዉን የምክር አገልግሎትና መረጃ በማስጠት በወቅቱ ወደ ጤና ተቋም በመላክ ህብረተሰቡን ከጤና ችግር ማታደግ አለበት፤

11. በሞዴል መድኃኒት ቤቱ ተገልጋይ ለሆኑ ስር በሰደደ በሽታ ለረጅም ጊዜ ለሚታከሙ ህሙማን ተከታታይነት ያለው መረጃ በመያዝ መድኃኒታቸዉን ከተገቢው የክትትል እና የምክር አገልግሎት እንደ አስፈላጊነቱ ሊሰጥ ይችላል፡፡

12. የጤና ማበልፀግና በሽታ መከላከል በተመለከተ ለህብረተሰቡ ትምህርት የማስጠት ኃላፊነት አለባቸው፡፡

13. የናርኮቲክና ሳይኮትሮፒክ መድኃኒቶች ለእዚህ ተብሎ በተዘጋጀዉ የመድኃኒት ማዘዣ ወረቀቶች ብቻ ሚደል አለበት፡፡

14. የመድኃኒት ጎጂ ባሕርያት፣ ከመድኃኒት ጋር የተያያዘ የህክምና ስሕተት እና የመድኃኒት የጥራት ጉድለት ሲያጋጥመው አግባብ ላለዉ አካል ሪፖርት የሚድረግ ኃላፊነት አለበት፡፡

15. ምንጩ የሚይታወቅ፣ የአገልግሎት ጊዜው ያለፈበት እና የተበላሸ ማንኛውም መድኃኒት ለተጠቃሚዎች ማስጠት የለበትም

16. ማንኛዉንም ሽያጭ ሲከናወን በገንዘብ ሚኒስቴር ተፈቅዶ በታተመ ደረሰኝ ብቻ መሸጥ አለበት

17. ለተገልጋዩ የመድኃኒቶቹን ዋጋ አስቀድሞ የማሳወቅ ግዴታ አለበት

ክፍል ስምንት
ስለመድኃኒት ቆጠራ፣ ሪፖርት አደራረግና ኦዲት

30. የመድኃኒት ቆጠራና ሪፖርት

1. ማንኛውም ሞዴል መድኃኒት ቤት በማዘን የሚገኙት መድኃኒቶች በየሩብ ዓመቱ እና በመድኃኒት ማደያ (ዲስፔንሰሪ) ክፍሎች የሚገኙ መድኃኒቶችን ደግሞ በየወሩ መቁጠር አለበት፡፡
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ እንደ አስፈላጊነቱ ማንኛውም የጤና ተቋም ድንገተኛ የመድኃኒት ቆጠራ ሊያካሂድ ይችላል፡፡
3. በዚሁ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) እና (2) የተገለጸው የቆጠራ ውጤት ከመድኃኒት መቆጣጠሪያ ማዝገቦች (ቢን ካርድ፣ ስቶክ ካርድ ወይም ዘመናዊ ሶፍት ዌር) እና ከሂሳብ ሪፖርት ጋር ተገናዝቦ በጤና ተቋሙ ለሚመለከታቸው አካላት ሪፖርት መደረግ አለበት፡፡

31. የሂሳብ እና የአገልግሎት ሪፖርት አቀራረብ ስርዓት

ማንኛውም የመድኃኒት ሂሳብ ባለሙያ፡ -

1. ለህሙማን የታደለ/ዲስፔንስ የተደረገ ማንኛውንም መድኃኒት እንደየ ሂሳብ መደቡ ለዚሁ ዓላማ በተዘጋጀው የዕለት የሂሳብ ማጠቃለያ ቅጽ መሰረት ሪፖርትማሰራት አለበት፡፡
2. በየወሩ የገቢ ወጪ መድኃኒቶችን ማጠቃለያ ሪፖርት ያቀርባል፡፡
3. በወሩ ወስጥ የተሸጠውን የመድኃኒት ዋጋ እና ጥቅም ላይ የሚውሉ መድኃኒቶችን በማየት ከውጭ ቀሪ ያለውን የመድኃኒት ዋጋ ከመድኃኒት ቤቱ ኃላፊ ጋር በማፀደቅ ለሚመለከታቸው አካላት ሪፖርት ማድረግ አለበት፡፡
4. የተስተናገደውን የተገልጋይ ቁጥር፣ የተሰጠውን አገልገሎት በዓይነት ጠቅሶ በወሩ ሚጨረሻ ሪፖርት ማድረግ አለበት፡፡

ማንኛውም የሞዴል መድኃኒት ቤት ኃላፊ

1. በመድኃኒት የሚቀፍ ግዥ ማዘርዝሩ የተካተቱ አከፋፋዮችን የአቅርቦት አፈጻጸም በየሩብ ዓመቱ ለሚመለከታቸው አካላት ማቅረብና ማጸደቅ እንዲሁም ለፌደራል ጤና ሚኒስቴር የሞዴል መድኃኒት ቤት ማስተባበሪያ አካል ማላክ አለበት
2. በመድኃኒት የሚቀፍ ግዥ ማዘርዝሩ የተካተቱ ነገር ግን በተለያዩ ምክንያቶች መቅረብ ያልቻሉ መድኃኒቶችን እና ጥቅም ላይ እንደማይወሉ የታወቁ መድኃኒቶችን ወዲያወኑ ለሚመለከታቸው አካላት ሪፖርት አቅርቦ እርምጃ እንዲወሰድ ማድረግ አለበት፡፡
3. አጠቃላይ የመድኃኒት ክፍሉን የሥራ እንቅስቃሴ በተመለከተ ለዚሁ ዓላማ በተዘጋጀ ሪፖርት ማድረጊያ ቅጽ መሰረት የጤና ተቋሙ የሂሳብ እና የአገልግሎት ሪፖርቱን ካጸደቀው በኋላ ይህንን ፕሮጀክት ለሚከታተለው የፌደራል ጤናሚኒስቴር አካል በየወሩ ማላክ አለበት፡፡

32. ጥቅም ላይ የማይውሉ መድኃኒቶች ሪፖርት አቀራረብና አወጋገድ

1. ማንኛውም የመድኃኒት ባለሙያ እንዲያስተዳድራቸው ከተመደቡለት መድኃኒቶች መካከል የአገልግሎት ጊዜያቸው ያለፈባቸው፣ የተበከሉ፣ ያለአግባብ የተከፈቱ፣ የቅዝቃዜ ሰንሰለት ያልጠበቁ፣ በተቆጣጣሪ አካል ጥቅም ላይ እንዳይውሉ የተከለከሉ እና በሌሎች ተመሳሳይነት ባላቸው ምክንያቶች ጥቅም ላይ የማይውሉ መድኃኒቶችን ያገኘ እንደሆነ አገልግሎት ከሚሰጡት ለይቶ በተመዘገበለት ባለሙያ ስም ማዝግቦ በየወሩ ለመድኃኒት ሂሳብ ባለሙያ እና ለሚመለከተው አካል ሪፖርት ማድረግ አለበት፡፡
2. የአገልግሎት ጊዜያቸው ያለፈባቸው እና አገልግሎት ላይ ሊውሉ የማይችሉ መድኃኒቶችና የህክምና ግብአቶችን አወጋገድ በተመለከተ በመድኃኒት አወጋገድ መመሪያ መሰረት መወገድ አለበት፡፡
3. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (2) የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ጥቅም ላይ የማይውሉ መድኃኒቶች የሚወገዱበትን ስርዓት (Disposal Facility) ማዘጋጀት አለባቸው፡፡

33. ኦዲት ስለማከደረግ

1. ማንኛወም ሞዴል መድኃኒት ቤት በመድኃኒት ቤቱ የሚከናወነወን የመድኃኒት ቅብበሎሽ ስርዓት እና አገልግሎት አሰጣጡን ቢያንስ በወር አንድ ጊዜ በተቋሙ የወስጥ ኦዲተር የናሙና ኦዲት ማከደረግ አለበት፡፡
2. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1) የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ ወደና ተፈላጊ መድኃኒቶች ኦዲት መደረጉበት አለባቸው፡፡
3. የሂሳብና የአገልግሎት ጠቅላላ ኦዲት ቢያንስ በየሦስት ወሩ በወስጥ ኦዲተር እና ቢያንስ በዓመት አንድ ጊዜ በወጭ ኦዲተር ኦዲት በማከደረግ በተቋሙ የበላይ ኃላፊና ለሞዴል መድኃኒት ቤቱ ሜጀመንት ኮሚቴ ማቅረብ አለበት፡፡
4. በኦዲት ወጤት ማሳረት ጉድለት የተገኘ ከሆነ እና መድኃኒቶች የአገልግሎት ጥቅም ላይ ሳይወሉ የአገልግሎት ጊዜያቸው ካለፈ ወይም ከተበላሹ ዋጋቸው ተሰልቶ ካልተጣራ ትርፍ ላይ ተቀናሽ ይሆናል፡፡

34. ስለ ክትትልና ግምገማ

1. የጤና ሚኒስቴር ሞዴል መድኃኒት ቤቶች ማስተባበሪያ አካል በየወሩ የሚቀበለውን ሪፖርት መሰረት በማድረግ ግብረ-መልስ መስጠት አለበት፡፡
2. የማስተባበሪያው አካል ቢያንስ በየስድስት ወሩ በስሩ በሚገኙ ሞዴል መድኃኒት ቤቶች በአካል በመገኘት ድጋፋዊ ክትትል ያደርጋል፡፡
3. የጤና ሚኒስቴር ቢያንስ በአመት አንድ ጊዜ ከሞዴል መድኃኒት ቤቶች እና ከአቅራቢዎች ጋር የጋራ የምክክር መድረክ በማዘጋጀት አፈጻጸማቸውን ይገመግማል፣ ጥሩ ተሞክሯቸውን እንዲለዋወጡ ያደርጋል፣ ለችግሮች መፍትሔ ያስቀምጣል፡፡

ክፍልዘጠኝ
የአስፈጻሚ አካላት ተግባርና ኃላፊነት

35. የጤና ሚኒስቴር ተግባርና ኃላፊነት

1. በሀገር አቀፍ ደረጃ የሞዴል መድኃኒት ቤት ፕሮጀክትን ይመራል፣ ይደግፋል፣ ይከታተላል፣ ለሚያጋጥሙ ችግሮች የመፍትሄ አቅጣጫ ይሰጣል፡፡
2. በሀገሪቱ ወስጥ በመድኃኒት አቅርቦት ላይ የተሰማሩ አስመጪዎችንና የአከፋፋዮችን አቅም አሟጦ ማጠቀም ይቻልዘንድ የሚቀፍ ግኙ ተግባራዊ እንዲሆን ሁኔታዎችን ያመቻቻል፣ ሂደቱን ይከታተላል፡፡
3. የጤና ሚኒስቴር ሞዴል ለመሆን ወል ለፈረሙ የከነሜ የቀይ መስቀልና የግል መድኃኒት ቤቶች ስልጠና እንዲያገኙ፣ ስራ ለማስጀመር መድኃኒት በዓይነት እንዲያገኙ፣ የጤና መድህን አገልግሎት ሰጪ አካል እንዲሆኑና የማስሰሉት ድጋፎች እንዲያገኙ ያመቻቻል፡፡
4. ከገንዘብ ሚኒስቴር ጋር በመመካከር የገቢ፣ የወጪ እና የሽያጭ ማስብሰቢያ ሰነዶችንና ቅጻቅጾች ተዘጋጅተው ስራ ላይ እንዲወሉና ወቅታዊ እንዲሆኑ ያደርጋል፡፡
5. በሞዴል መድኃኒት ቤት አሰራር ዙሪያ ለሚሳከታቸው ሃላፊዎችና ባለሞያዎች ስልጠና ለመስጠት የስልጠና ማኑዋሎችን ያዘጋጃል፣ አሰልጣኞች ይመድባል ሌሎች ግብዓቶችንም በማሟላት ስልጠናእንዲያገኙ ያደርጋል፡፡
6. በመድኃኒት አገልግሎት አሰጣጥና ስርጭት ተግባር ላይ ለተሰማሩ ሰራተኞችና ባለሞያዎች የጉድለት ተጋላጭነት ማካካሻ እና ሌሎች ጥቅማጥቅሞች በመመሪያ እንዲፈጸም ያደርጋል፡፡
7. በፌዴራል ሆስፒታሎች ስር በሚቋቋሙ ሞዴል መድኃኒት ቤቶች የመድኃኒት አቅርቦትና አጠቃቀም የኦዲት ሪፖርቶችን በአመት አንድ ጊዜ ይገመግማል፤ በወጡቱ መሰረት ተገቢውን እርምጃ ይወስዳል፡፡
8. ጥቅም ላይ የማይወሉ መድኃኒቶች በመድኃኒት አወጋገድ መመሪያ መሰረት እንዲወገዱ ለሞዴል መድኃኒት ቤቶች አስፈላጊውን ድጋፍ ያደርጋል፡፡
9. በሀገር አቀፍ ደረጃ የሞዴል መድኃኒት ቤት ፕሮጀክት ትግበራን አቅርቦትንና አገልግሎትን ከማሻሻልና ገበያን ከሚረጋጋትና መገራት አንጻር እያበረከተ ስላለው አስተዋጽኦ የዳሰሳ ጥናት ያካሂዳል፤ በተገኘው ወጤት መሰረትም የማስተካከያ እርምጃ ይወስዳል፡፡
10. የከነሜ የቀይ መስቀልና የግል መድኃኒት ቤቶች በሞዴልነት እንዲስፋፉ ያበረታታል፤ ሞዴል ለመሆን ወል ለፈረሙት ስልጠና እንዲያገኙ፣ ስራ ለማስጀመር የሚሆን መድኃኒት በዓይነት እንዲያገኙ፣ በጤና መድህን ስርዓት እንዲታቀፉና የማስሰሉትን ድጋፎች እንዲያገኙ ያደርጋል፡፡
11. ስለ ሞዴል መድኃኒት ቤቶች አሰራርና አገልግሎት ለህብረተሰቡ ያስተዋወቃል፡፡
12. ሞዴል መድኃኒት ቤቶች በዚህ መመሪያ በተቀመጠው የትርፍ ወሰን መሰረት ሽያጭ ማከናወናቸውን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፡፡

36. የመድኃኒት አቅርቦት ኤጀንሲ ተግባርና ኃላፊነት

1. ለሞዴል መድኃኒት ቤቶች ስራ ለማስጀመር የመነሻ ካፒታል በዓይነት በዱቤ ይሰጣል፡፡
2. ያለምንም መቆራረጥ ሊያቀርባቸው የሚችላቸውን መድኃኒቶች ዝርዝር ከነ ቅንጣት ዋጋቸው ጋር በአመቱ መጀመሪያ ላይ ለሚመለከታቸው አካላት ማሳወቅ፡፡
3. ለሚያቀርባቸው መድኃኒቶች ቀደም ብሎ በሚቀፍ ግዥ አሰራር ስርዓት ማስረት ከአሸናፊ አቅራቢዎች ጋር ስምምነት በማድረግ ያሸነፉ አቅራቢዎችን፣ የመድኃኒቶችን ዝርዝርና ያሸነፉበትን የቅንጣት ዋጋ ኮድ አድርጎ ማሳወቅ፡፡
4. አቅራቢዎቹ በውል ስምምነቱ ማስረት ሚጸማቸውን ይከታተላል፣ ድጋፍ ያደርጋል፣ በአግባቡ ካልተፈጸመ ተለዋጭ መፍትሔ ይሰጣል፡፡
5. የመድኃኒት አቅርቦት ኤጀንሲ ያለምንም መቆራረጥ ሊያቀርባቸው የሚችላቸውን መድኃኒቶች ዝርዝር ከነ ቅንጣት ዋጋቸው እና ከሚያቀርብላቸው ሞዴል መድኃኒት ቤቶች ዝርዝር ጋር በአመቱ መጀመሪያ በፌደራል ደረጃ ለሚቋቋመው የሞዴል መድኃኒት ቤቶች ማስተባበሪያ አካል ያቀርባል፡፡
6. መድኃኒት አቅርቦት ኤጀንሲ ለሚያቀርባቸው መድኃኒቶች ቀደም ብሎ በሚቀፍ ግዥ አሰራር ስርዓት ለበጀት ዓመቱ በኤጀንሲው በሀገር አቀፍ ደረጃ ከሚለዩ አስመጪዎችና አከፋፋዮች ሞዴል መድኃኒት ቤቶቹ በቀጥታ ግዥ ማከናወን ይችላሉ፡፡
7. የመድኃኒት አቅርቦት ኤጀንሲ ጨረታውን በመተንተን ያሸነፉ አቅራቢዎችን፣ የመድኃኒቶችን ዝርዝርና ያሸነፉበትን የቅንጣት ዋጋ ኮድ አድርጎ ለተጠቃሚ መድኃኒት ቤቶች እና ለሚመለከታቸው ሁሉ ይፋ ያደርጋል፤ የዋጋ ለውጥ በሚኖርበት ጊዜ ዋጋ ለቀየረው መድኃኒት ብቻ እንደገና በማጫረት አዲሱን የዋጋ ተመን ይፋ ያደርጋል፡፡
8. የመድኃኒት አቅርቦት ኤጀንሲ ጨረታውን ካሸነፉት አቅራቢዎች ጋር የሚቀፍ ግዥ ውል ስምምነት በሚፈራረም ሞዴል መድኃኒት ቤቶቹ ከአሸናፊ ድርጅቶች በተጠቀሰው የቅንጣት ዋጋ የጨረታው ዓመት እስኪጠናቀቅ ድረስ መግዛት እንደሚችሉ በግልጽ ደብዳቤ ያሳውቃል፡፡
9. በቅርንጫፍ መ/ቤቶች (PSA Hub) በኩል በክልል ጤና ቢሮ ስር ለሉ ሆስፒታሎች ተመሳሳይ አገልግሎት ይሰጣል፡፡

37. የሆስፒታሎች ተግባርና ኃላፊነት

1. ሆስፒታሉ ሞዴል መድኃኒት ቤት ከመከፈቱ በፊት በሆስፒታሉ ወስጥ የሚገኘውን ተመላላሽ መድኃኒት ቤት ሞዴል የማድረግ ኃላፊነት አለበት፡፡
2. ለሞዴል መድኃኒት ቤቱ የመድኃኒት ግዥን የሚፈፀመና የሚከበው የፋርማሲ ባለሙያ የተለያዩ እንዲሆኑ ያደርጋል፡፡
3. በሞዴል መድኃኒት ቤቱ መድኃኒት መጋዘን በዓመት አራት ጊዜ አጠቃላይ ቆጠራ እንዲካሄድ ያደርጋል፡፡
4. በየወሩ ከሚያገኘው የፋይናንስና የአገልግሎት ሪፖርት ላይ በመመስረት ግብረ-መልስ ይሰጣል፡፡

5. በሞዴል መድኃኒት ቤቶች ወስጥ የሚሰሩ የመድኃኒት ባለሞያዎች በጋራ የሚሰራት፣ መድኃኒቶን በጋራ የሚስተዳደር፣ የማከባከብ እና የጋራ ሀላፊነትና ተጠየቂነትን የሚያሰፍን የአሰራር ስርዓት ይዘረጋል፤ ተግባራውነቱንም ይከታተላል፡፡

6. በሞዴል መድኃኒት ቤቶች የመድኃኒት አቅርቦትና አጠቃቀም በየሶስት ወሩ በወስጥ አዲተር እና በአመት አንድ ጊዜ በውጭ አዲተር ኦዲት መደረጉን ያረጋግጣል፤ በኦዲት ወጤቱ ማስረት ተገቢወን እርምጃ ይወስዳል፡፡

7. ሆስፒታሉ በሚያቋቁማቸው ሞዴል መድኃኒት ቤቶች ይህን መመሪያ ተግባራዊ እንዲሆን ያደርጋል፡፡

8. ሆስፒታሉ የመድኃኒት አገልግሎቱ ቀልጣፉ እና ወጤታማ እንዲሆን በዚህ መመሪያ እና በሀገር አቀፍ ደረጃ በወጣው ማስፈርት ማስረት የመድኃኒት ማጋዝኖችን እና የሚዲያ ክፍሎችን ሚደራጀት፣ የሰው ሀይል እና ቁሳቁሶችን ማሟላት አለበት

9. ደንበኞች መድኃኒቶችን በአግባቡ እንዲይዙ የሚዩዙበትን ማሸግያ ሆስፒታሉ ማቅረብ አለበት

10. ሆስፒታሉ ስለመድኃኒት አገልግሎት የሚሊሉ ሪፖርቶችን በየወሩ፣ በየሩብ ዓመቱ እና በየአመቱ የሚጠቃለያ ሪፖርት ሰምቶ የሚጠናከሪያ እና የሚስተካከያ እርምጃ መወሰድ አለበት፡፡

38. የሞዴል መድኃኒት ቤት ማኔጅመንት ኮሚቴ ተግባር እና ኃላፊነት

1. የየወሩን የመድኃኒት ግዥና ሽያጭ እና የአገልግሎት አሰጣጥ ሪፖርት ያዳምጣል፣ ይገመግማል፣ ለችግሮች ወቅታዊ መፍትሄ ይሰጣል፤
2. በሞዴል መድኃኒት ቤት የሚሰሩ ሰራተኞችን ቅጥር ይከታተላል፡፡
3. የሞዴል መድኃኒት ቤቶች አተገባበር መመሪያ በአግባቡ ሚፈጸማ ይከታተላል፡፡
4. የገቢና ወጭ ሰነዶች፣የገንዘብ ማስብሰቢያ ደረሰኞች እና ሌሎች ቅፃቅፆች በወቅቱ መታተማቸወን እና ለስራ ዝግጁ መሆናቸወን ይከታተላል፡፡
5. የሞዴል መድኃኒት ቤቱ የራሱ የሆነ የባንክ አካወንት እንዲከፍት ያደርጋል፤ አጠቃላይ የሂሳብ እንቅስቃሴወን ይመራል፣ ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል
6. የኦዲት ሪፖርቶችን ይሚያምራል፣ ከሚያሚከታቸው ሰራተኞች ጋር ይወያያል፣ ወሳኔዎችን ያስተላልፋል፤ ተግባራዊነታቸወን ይከታተላል

39. የሆስፒታል ቦርድ ተግባርና ኃላፊነት

1. በሆስፒታሉ ሞዴል መድኃኒት ቤቶች ወስጥ የሚከሄደወን እቅስቃሴ በተሟላ ደረጃ እንዲተገበር ለሆስፒታሉ ተገቢወን ድጋፍ እየሰጠ፣ ክትትል ያደርጋል፣ ወሳኔ ይሰጣል፡፡
2. የሆስፒታሉን የመድኃኒት በጀት አቅም የሚሳለብትበትን ሁኔታ ያመቻቻል፡፡

3. በመድኃኒት አገልግሎት አሰጣጥና ስርጭት ተግባር ላይ ለተሰማሩ ሰራተኞችና ባለሞያዎች ጥቅማ ጥቅሞች በመሚያው ማስረት እንደሚዝገበር ክትትል በማድረግ ያረጋግጣል::

4. በማግስት ግዥና ንብረት አስተዳደር ፖሊሲዎች፤ መርሆዎችና አፈጻጸሞች ማስረት የመድኃኒት አገልግሎት አሰጣጡን በተማለከተ ሂደቱን ይቆጣጠራል፣ አመራር ይሰጣል፣ ተግባራዊነቱን ይከታተላል፣ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ህጋዊ እርምጃ እንዲወሰድ ያደርጋል፡፡

5. በሞዴል መድኃኒት ቤት የመድኃኒት አቅርቦትና አጠቃቀም ኦዲት በየሶስት ወሩ በወስጥ ኦዲተር እና በአመት አንድ ጊዜ በወጭ ኦዲተሮች ኦዲት መደረጉን ይከታተላል፤ ያረጋግጣል፡፡

40. የሞዴል መድኃኒት ቤት ኃላፊ ተግባርና ኃላፊነት

1. ከአስተደደር ጋር ቀጥታ ግንኙነት የሚደረግ፣ ወደ ተለያዩ የተቋሙ ክፍሎች የመግባትና ከሚሰጠው አገልግሎት ጋር የተያያዙ ሰነዶችን መቆጣጠር፤
2. ስለ እያንዳንዱ ባለሙያ የስራ ድርሻ ኃላፊነት የሚገልጽ ሰነድ ማዘጋጀትና ሁሉም ባለሙያዎች የመድኃኒትና ሕክምና መገልገያ ጥራትና ደህንነትን ሊጠብቁ የሚችሉ ስልጠናዎች እንዲያገኙ ማድረግ፤
3. የድርጅቱን የመድኃኒት ክምችት እና አጠቃላይ የመድኃኒት ዕደላ ስርአት የመከታተልና የጥራት፣ የደህንነት እና የፈዋሽነት ችግሮችን የመቆጣጠር ሀላፊነት አለበት
4. የናርኮቲክ እና ሳይኮትሮፒክ መድኃኒቶችና ሰነዶች ቁልፍ ባለው ቁምሳጥን ወይም የተለየ ክፍል ቆልፎ የሚያዝ
5. የቅድመ ምረቃ ተማሪዎች የሚማሩት ትምህርት በተግባር እንዲለማመዱ ሲፈቀድ የቅርብ ክትትል ማድረግ፤
6. የሚወጡ አገር አቀፍ ደረጃዎችንና መመሪያዎችን የመተግበርና የማስተግበር ግዴታ፤
7. ያልተፈቀደለት ማንኛውም ሰዉ ወደ ሚዲያና ማከማቻ ክፍል እንዳይገባና የማዘዝንና የክምችት ቁጥጥር በተገቢዉ መንገድ መከናወኑን ማረጋገጥ፤
8. መደርደሪያዎችንና ማከማቻ ቦታዎችን ለማፅዳ ሰዉ ማድረግ ያለበትን ጥንቃቄ ማሳወቅ፤
9. በስሩ የሚገኙ ባለሙያዎች የሙያ ወሰን በሚፈቅድላቸው አገልግሎት እንዲሰጡ የሚደረግ
10. በቅመማ ሚዲያ፣ የምክር አገልግሎትና በማከማቻ ክፍል ወስጥ መበላት፣ ማጠጣት፣ ሲጋራ ማጨስ ወይም ሌሎች ንፅህናን የሚጎዱ ተግባራትን እንዳይከናወን ማድረግ፤ እና
11. ከሙያው ጋር በተያያዘ ለሚፈጠር የአሰራር ግድፈት ኃላፊነት አለበት፡፡

ክፍል አስር
ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

41. ስለቅጣት

በዚህ መመሪያ የተጠቀሱትን ድንጋጌዎች የተላለፈ ማንኛውም ሰው አግባብ ባለው ህግ መሰረት ይቀጣል፡፡

42. ስለ ቅሬታ አቀራረብ

1. ማንኛውም ቅሬታ ያለው ሰው ቅሬታውን በመጀመሪያ ለሞዴል መድኃኒት ቤቱ ኃላፊ እንዳስፈላጊነቱ በቃል ወይም በፅሑፍ ማቅረብ አለበት፡፡

2. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1) መሰረት አጥጋቢ ምላሽ ያላገኘ ሰው ወደ ቀጣዩ የአደረጃጀት እርከን ቅሬታውን የማቅረብና መፍትሔ የማግኘት መብት አለው፡፡

43. ስለ ዱቤ ክፍያ

የመድኃኒት አቅራቢ ድርጅቶች ላቀረቡት መድኃኒት በአንድ ወር ጊዜ ወስጥ ክፍያ ከሆስፒታሉ ይቀበላሉ፤ በዱቤና በጤና መድህን ሽፋን ለተሸጡ መድኃኒቶች ክፍያ ሞዴል መድኃኒት ቤቱ በየወሩ እንዲሰበሰቡ የማድረግ ኃላፊነት አለበት፡፡

44. ህገ ወጥ የመድኃኒት ዝውውርን ስለመከላከል

ማንኛውም ሞዴል መድኃኒት ቤት፡ -

1. የሚገዛቸው መድኃኒቶች ከህጋዊ ምንጭ መሆናቸውን ማረጋገጥ አለበት፡፡
2. ለሚገዛቸው መድኃኒቶች ህጋዊ የግዥ ደረሰኝ እና በአደራ ለሚከባቸው ደግሞ ህጋዊ የአደራ መረከቢያ ቅጽ በመጠቀም መሆን አለበት፡፡
3. አስፈላጊው ሕጋዊ ሰነድ ባልተሟላበት ሁኔታ ምንም ዓይነት መድኃኒት ለታካሚ መስጠት የለበትም፡፡
4. ምንጫቸው የማይታወቅ ወይም ህጋዊ ካልሆኑ ምንጮች የተገኘ መድኃኒት ሲያጋጥም ወዲያውኑ ለአካባቢው ፖሊስ እና አግባብ ላለው ተቆጣጣሪ አካል ማሳወቅ አለበት፡፡
5. የመድኃኒት ዝውውር ሲያከናውን የመድኃኒት ዝውውር አፈፃፀም መመሪያ መሰረት የመድኃኒቶችን የገቢና ወጪ ስርዓት ተከትሎ መሆን አለበት፡፡

45. ቅፃቅጽ

ከዚህ መመሪያ ጋር ተያይዘው የቀረቡ ቅፃቅጽ የህግ አስገዳጅነት ይኖራቸዋል፡፡

46. ስለ መተባበር ግዴታ

ይህ መመሪያ ተፈፃሚ እንዲሆን ጉዳዩ የሚመለከታቸው አካላት የመተባበር ግዴታ አለባቸው፡፡

47. መመሪያው ስለሚሻሻልበት ሁኔታ

ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ይህንን መመሪያ አስፈላጊ ሆኖ ባገኘበት ጊዜ ሊያሻሻለው ይችላል፡፡

48. ተፈፃሚነት የማይኖራቸው ህጎች

አግባብ ያለው ተቆጣጣሪ አካል ያወጣቸው መመሪያዎች እንደተጠበቁ ሆነው ይህንን መመሪያ የሚቃረን ማንኛውም መመሪያ ወይም የተለመደ አሰራር ወይም ሰርኩላር ደብዳቤ በዚህ መመሪያ ውስጥ የተመለከቱ ጉዳዮችን በሚመለከት ተፈፃሚነት አይኖረውም፡

49. መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ በሚኒስትሩ ከተፈረመበት ጊዜ ጀምሮ ተፈፃሚ ይሆናል

ጥር 2011 ዓም፣ አዲስ አበባ

ዶ/ር አሚር አማን

የጤና ሚኒስቴር ሚኒስትር

እዝል 1፡ አስፈላጊ የሚዲያ ክፍልና የስቶር ግብዓቶች

1. የመድኃኒት መደርደሪያዎች ወይም ፓሌት፤
2. በቀላሉ መጽዳት የሚችል ባንኮኒ፤
3. የናርኮቲክና ሳይኮትሮፒክ መድኃኒቶች የሚቀመጡበት ባለቁልፍ ቁምሳጥን ወይም የብረት ካቢኔት፤
4. ማቀዝቀዣ መሳሪያ ከነሙቀት መቆጣጠሪያ ቴርሞ ሜትር፤
5. የግድግዳ ሙቀት መቆጣጠሪያ መሳሪያ በመድኃኒት ሚዲያና ማከማቻ ክፍል፤
6. መድኃኒት ቤቱ ከፍተኛ ሙቀት ባለበት አከባቢ የሚገኝ ከሆነ መድኃኒት ያሉባቸውን ክፍሎች በሚያዳርስ ሁኔታ አየር ኮንድሽነር (AC) ወይም ቬንትሌተር፤
7. የተገልጋዮች ማረፊያ ወንበሮች፤

8. የእሳት አደጋ ማጥፊያ መሣሪያ፤
9. ለጽሕፈት አገልግሎት የሚውል ጠረጴዛ፣ እስቶክና ቢን ካርድ
10. ማጣቀሻ መጻሕፍት ቢያንስ ሀገራዊ የመድኃኒት ፎርሙላሪ (ማዘርዝር)፣ የመድኃኒት ዕደላ ስርዓት ማንዋል (Good Dispensing Manual)፣ አንድ ወጥ የህክምና ጋይድላይን (Standard Treatment Guideline)፤
11. እንደአስፈላጊነቱ የቁመትና ክብደት ማለኪያ፣ የደም ግፊት ማለኪያ፣ የስኳር ማጠን ማለኪያ
12. የመድኃኒት ሟደያ ከረጢት (Envelop)

እዝል 2፡ አስፈላጊ የቅመማ ቁሳቁሶች

ዝርዝር ብዛት

1. Prescription Balance-- 1
2. Glass/porcelain Mortar and pestel-- 1
3. Graduated measuring cylinders (Different size)--- 2
4. Beakers of different sizes-- 4
5. Spatula---2
6. Ointment title---1
7. Glass rods-- 2
8. Funnel (Glass or plastic)-- 2

9. Flask of different sizes--2
10. Test tubes of different size--2
11. Packing materials--Enough amount
12. Water filter (candle filter)---1

እዝል 3፡ አስራ አምስት በመቶ (15%) ከስራዉ ጋር ግንኙነት ላላቸዉ የአስተዳደር አካላት እና ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች ክፍፍል ዝርዝር

ተ.ቁ	የስራ ድርሻ	ክፍፍል በፐርሰንት (%)
1	የተቋሙ ኃላፊ ወይም የመድኃኒት ቤቱ ማኔጅመንት ኮሚቴ ሰብሰቢ	1.5
2	የዕለት ገንዛብ ሰብሰቢ	2
3	የመድኃኒት ቤቱ አካውንታንት	2
4	ፋይናንስ ኃላፊ/አስተዳደር እና ልማት ዳይሬክተር	1
5	ዋና ገንዛብ ያዥ	0.5
6	የኦዲት ኃላፊ	1
7	የኦዲት ባለሙያዎች	1
8	የጽዳት ሰራተኞች	0.5
9	የጥበቃ ሰራተኞች	1
10	የጉልበት ሰራተኞች	0.5
11	የግዥ ኃላፊ	1
12	የጨረታ ኮሚቴ እና አጽዳቂ ኮሚቴ	1.5

13	የሰው ሀብት ኃላፊ	0.5
14	ሌሎች ከስራው ጋር ጉንኙነት ያለቸው ሰራተኞች	1
	ጠቅላላ ድምር በፐርሰንት	**15%**